# እንኳን ደህና መጣችሁ




የህዳር /2018 ዓ.ም

# ከተከፋይ ሂሳቦች ላይ ታክስ ቀንሶ የማስቀረት አስተዳደር ሥርዓት ማሰልጠኛ ሞጁል

# ይዘት

ክፍል አንድ - አጠቃላይ ሁኔታ

ክፍል ሁለት-ከተከፋይ ሂሳቦች ላይ ግብርን ቀንሶ ማስቀረት

ክፍል ሶስት - ቅድመ ታክስ /withholding tax/

ማጠቃለያ

ማጣቀሻ

# ክፍል አንድ

## አጠቃላይ ሁኔታ

### 1.1 ዋና ዓላማ

- ግብር ከፋዮች/ደንበኞች ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብር ቀንሶ ስለማስቀረትን መሠረታዊ/ዋና የህግ ደንጋጌዎችንና አስተዳደር ሥነ-ስርዓቶች ላይ ግንዘቤ በመፍጠር መብታቸውን በማስከበር ግዴታቸውን እንዲወጡ ማድረግ ፡፡

# ከተከፋይ ሂሳቦች ላይ ግብርን ቀንሶ ስለማስቀረት ሥርዓት

## 2.1. ከመቀጠር ከሚገኝ ገቢ ላይ ግብርን ቀንሶ ስለማስቀረት

- ማንኛውም ቀጣሪ ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ ግብር የሚከፈልበትን ለተቀጣሪው በሚከፍልበት ጊዜ ከ15% እስከ 35% ባለው የማስከፈያ መጣኔ መሠረት ከጠቅላላው ክፍያ (ደመወዝ፤ ከታክስ ነጻ ያልሆኑ የተለያዩ ክፍያዎች እና ግብር የሚጣልበት የዓይነት ጥቅም) በማስላት ቀንሶ በማስቀረት ለታክስ ባለሥልጣኑ አሳውቆ መክፈል ይኖርበታል ፡፡

# ከተከፋይ ሂሳቦች ላይ.......

- ከራስ ገቢ ላይ ግብር ቀንሶ ስለመያዝ፡- በዓለም አቀፍ ድርጅት የተቀጠረ ወይም በኢትዮጵያ ውስጥ ባለ የውጭ አገር ኤምባሲ፤ ድፕሎማቲክ ሚሽን፤ ወይም ሌላ ኮንሱላር ተቋም ተቀጥሮ የሚሰራ ሰው ወይም በማናቸውም ህግ ከመቀጠር ከሚገኝ ገቢ ላይ ግብር ቀንሶ የማስቀረት ግዴታ ለሌለበት ቀጠሪ የሚሰራ ሰው ከእነዚህ ተቋማት ከሚቀበለው ከመቀጠር ከሚገኝ ገቢ ላይ ግብር ቀንሶ የመያዝ እና የማሳወቅ ግዴታ አለበት ፡፡

# ከተከፋይ ሂሳቦች ላይ.......

2.2 በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው/ድርጅት ግብር የሚከፈልበት መጣኔ፡-

- ከመድን አርቦን15%
- ከሮያሊቲ ጠቅላላ ክፍያ ላይ---- 10%
- ከትርፍ ድርሻ 15%
- ከወለድ ጠቅላላ ገቢ ላይ---------- 10%
- ከስራ አመራር ክፍያና ከቴክኒክ አገልግሎት ጠቅላላ ክፍያ ላይ......15%
- የመዝናኛ አገልግሎት ሰጪዎች ግብር ---------- 15%
- የዓለም አቀፍ አየር ትራንስፖርት ድርጅቶች ግብር---- 3%
- የማዕድንና ፔትሮሊየም ገቢ ግብር------------- 25%

# ከተከፋይ ሂሳቦች ላይ.......

**2.3 በኢትዮጵያ ነዋሪ ለሆኑ ወይም ኢትዮጵያ ውስጥ በቋሚነት ለሚሰራ ድርጅት፡-**

- ሮያልቲ............ 10%
- የሮያልቲ ገቢው የተገኘው ከኪነጥበብ ወይም ከባህላዊ ስራ ከሆነ 5% (አምስት በመቶ)፤ የገቢ ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት።
- የትርፍ ድርሻ....... 15%
- በሌላ ማናቸውም ሁኔታ ከሚገኝ ወለድ ግብር .....10%
- ከዕድል ሙከራ የሚገኝ ገቢ ግብር ............ 25%

# ከተከፋይ ሂሳቦች ላይ.......

- ሃብትን አልፎ አልፎ በማከራየት የሚገኝ ገቢ (መሬት፣ቤት፣ የሚንቀሳቀስ ሃብት...) በማከራየት የሚገኝ ገቢ ላይ ግብር ---15%
- **የካፒታል ሀብቶችን በማስተላለፍ በሚገኝ ጥቅም ላይ ግብር ስለመጣል**
  - አንድ ሰው ግብር የሚከፈልበት ሀብት ተብሎ የሚጠቀስን በምድብ ‘ሀ’ (የማይንቀሳቀስ ሀብት)---- 15%
  - ምድብ ‘ለ‘ (አክስዮን ወይም ቦንድ) በማስተላለፍ ጥቅም ያገኘ እንደሆነ በተገኘው ጥቅም ላይ -----15% ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

# ከተከፋይ ሂሳቦች ላይ.......

- ግብር የሚከፈልበትን ሃብት በማስተላለፍ የሚገኝ ጥቅም ነው የሚባለው በሚከተለው ቀመር

ተሰልቶ የሚገኘው ጥቅም ነው፡-

ሐ - (ሀ + ለ) = ግብር የሚከፈልበት ጥቅም

ለዚህ ቀመር አፈፃፀም፦

ሀ - ሀብት የተፈራበት/የተገዛበት ዋጋ

ለ - የዋጋ ንረት ማስተካከያ 30% (ሠላሳ በመቶ)

ሐ - ሀብቱ የተላለፈበት ዋጋ

# ከተከፋይ ሂሳቦች ላይ.......

- የንግድ ድርጅት ሲተላለፍ ሊቀርብ የሚገባ ሰነድ
  - ከድርጅቱ ጋር አብረው የሚተላለፉ ንብረቶችን የመዝገብ ዋጋ የሚያሳይ ማስረጃ ፤
  - ግብር ከፋዩ የሚተላለፉ ንብረቶች ዋጋ የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ ካልተቻለ አግባብነት ያለው ፍቃድ በተሰጠው ንብረት ገማች የተገመተውን ንብረቱ የተገዛበትን ዋጋ ማቅረብ ይኖርበታል ፡፡

# ከተከፋይ ሂሳቦች ላይ.......

- ሀብትን በማስተላለፍ የሚገኝ ገቢን ለማስላት የሚቀርቡ ማስረጃዎች
  - የሂሳብ መዝገብ የሚይዝ ግብር ከፋይ ለካፒታል ሀብቱ የተደረገውን ወጪ የሚከተሉትን ማስረጃዎች በማቅረብ መረጋገጥ ይኖርበታል ፡፡
    - ✓ ለሀብቱ የተደረገውን ወጪ እና ሀብቱ የተገኘበትን ጊዜ የሚያሳይ ሰነድ
    - ✓ ሀብቱ ከተገኘበት ጊዜ ጀምሮ ስለእርጅና በጠቅላላው ተቀናሽ የተደረገውን ገንዘብ የሚያስረዳ ሠነድ ፡፡

# ከተከፋይ ሂሳቦች ላይ.......

- ግብር ከፋዩ ሀብቱን በማስተላለፍ ያገኘውን ገቢ አግባብነት ባለው ማስረጃ ማረጋገጥ ያለበት ሲሆን ፤ በቀረበው ማስረጃ መሠረት ግብሩ የሚከፈለው ማስረጃው በባለሥልጣኑ ተቀባይነት ሲያገኝ ነው ፡፡
- ለካፒታል ሀብቱ ስለተደረገው ወጪ እና የካፒታል ሀብቱን በማስተላለፍ ስለተገኘው ገቢ ግብር የቀረበው ማስረጃ በባለሥልጣኑ ዘንድ ተቀባይነት ያላገኘ እንደሆነ የወቅቱ እና የቦታው መደበኛ የገበያ ዋጋ) መሠረት የካፒታል ሀብትን በማስተላለፍ የተገኘውን ጥቅም ይሰላል ፡፡

# ከተከፋይ ሂሳቦች ላይ.......

- የሂሳብ መዝገብ ያልያዘ ወይም እንዲይዝ ግዴታ የሌለበት ግብር ከፋይ ሀብቱ የተገኘበትን ዋጋ በሚመለከተው አካል አስገምቶ እንዲቀርብ ያደርጋል ። ሆኖም ግብር ከፋዩ ይህን አስገምቶ ካለቀረበ ግብር ከፋዩ ወጪ እንደሌለው ይቆጠራል ።
- ለዚህም አፈጻጸም አግባብነት ያለው ማስረጃ ማለት ከሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት የሚቀርብ ውል ሲሆን በውሉ ላይ የተጠቀሰው የመሸጫ ዋጋ ተቀባይነት የሚያገኘው ከወቅቱ የገበያ ዋጋ ጋር ተመጣጣኝ ሆኖ ሲገኝ ነው ።

# ከተከፋይ ሂሳቦች ላይ.......

## 2.4 ባልተከፋፈለ ትርፍ ላይ ግብር የሚከፈልበት ሥርዓት

- ግብሩን ስለመክፈል፡-
  - ያልተከፋፈለ ትርፍ በአንድ የግብር ዓመት ግብር ከተከፈለ በኋላ ለአባላቱ ያልተከፋፈለ እና መልሶ ኢንቨስት ያልተደረገ የተጣራ የድርጅቱ ትርፍ 15% (አስራ አምስት በመቶ) ግብር ይከፈልበታል ፡፡

# ከተከፋይ ሂሳቦች ላይ.......

- አንድ ድርጅት ባልተከፋፈለ ትርፍ ላይ ግብር እንዲከፍል የማይጠየቀው ድርጅቱ የሂሳብ ጊዜው በተጠናቀቀ በ12 ወራ ጊዜ ውስጥ የአባላቱን የአክስዮን ድርሻ መጠን እና የድርጅቱን ካፒታል በተገኘው የተጣራ ትርፍ መጠን ልክ ካሳደገ ነው ።
- ሆኖም የተጣራው ትርፍ ያልተከፋፈለ ትርፍ ድርሻ ከፊል ከሆነ ባልተከፋፈለው የትርፍ መጠን ላይ ብቻ ይሆናል ።
- ያልተከፋፈለ ትርፍ ያለው ድርጅት የ12 ወራት ጊዜ ካበቃ በኃላ ባለው ሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ግብሩን አስታውቆ መክፈል ይኖርበታል ።

# ከተከፋይ ሂሳቦች ላይ.......

- ማስረጃዎችን ስለማቅረብ
  - አንድ ድርጅት ያልተከፋፈለ ትርፍ  የሌለው መሆኑን የሚወሰነው ፡-
    - ✓ አንድ ድርጅት በአንድ የሂሳብ ጊዜ ውስጥ የተገኘውን የተጣራ ትርፍ ለባለ አክስዮኖች የተከፋፈለ ወይም የባለ አክስዮኖቹን የአክስዮን ድርሻ መጠን ለማሳደግ የዋለ መሆኑን የሚያረጋግጡ እንደ ቅድመ ተከተላቸው በተከፋፈለው የትርፍ ድርሻ መጠን ልክ ግብር ስለመከፈሉ ወይም የድርጅቱ ካፒታል ስለማሳደጉ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ፤

# ከተከፋይ ሂሳቦች ላይ.......

- ✓ የአባላት የአክስዮን ድርሻ እና የድርጅቱ ካፒታል ስለማደጉ የሚቀርቡ ማስረጃዎች እንደአግባብነቱ ከሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት ወይም የክልል/ከተማ አስተዳደር የጸደቀ የድርጅቱ ቃሌ ጉበኤ እና ከንግድና ኢንድስትሪ ሚ/ር ወይም አግባብነት ካለው አካል/ የንግድ ቢሮ የድርጅቱ ካፒታል ስለማደጉ የሚገልጽ ሠነድ፤

# ከተከፋይ ሂሳቦች ላይ.......

- ድርጅቱ በ12 ወራት ጊዜ ውስጥ ያገኘውን የተጣራ ትርፍ ለባለ አክስዮኖች ሳያከፋፍል የአክስዮን ድርሻቸውን መጠን ለማሳደግ የዋለው ከሆነ ይሄንኑ የሂሳብ ጊዜው ካበቃ በኃላ ያለው 12 ወራት ከተጠናቀቀ በኃላ ባለው 2 ወር ወይም ቀደም ባለው ጊዜ ውስጥ አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎችን በማያያዝ ለባለሥልጣኑ ማስታወቅ አለበት ፡፡

# ከተከፋይ ሂሳቦች ላይ........

➢ **ባልተከፋፈለ ትርፍ ላይ ግብር ያለመክፈል ውጤት፡-**

- አንድ ድርጅት ያልተከፋፈለ ትርፍ ኖሮት በጊዜው ውስጥ ግብሩን ያላስታወቀ እና ያልከፈለ እንደሆነ ከሚከፍለው ፍሬ ግብር በተጨማሪ አስተዳደራዊ መቀጫ ይጣልበታል፤ እንዲሁም ባልተከፋፈለ ፍሬ ግብር ላይ ወለድ ይከፍልበታል ።

- አንድ ድርጅት የድርጅቱን ትርፍ የባለአክስዮኖችን ድርሻ ለማሳደግ የዋለው ሆኖ በህጉ መሠረት ያላስታወቀ እንደሆነ፤የታክስ ማስታወቂያ ሳያቀርብ ለዘገየበት ለእያንዳንዱ የታክስ ጊዜ አሥር ሺህ ብር (10000.00 ብር) አስተዳደራዊ መቀጫ ብቻ ይጣልበታል ።

# ከተከፋይ ሂሳቦች ላይ…….

- **በግብር እፎይታ ላይ ያለ ድርጅት**

- የግብር እፎይታ ላይ ያለ ድርጅት ያገኘውን የተጣራ ትርፍ ለባለ አክስዮኖች ካከፋፈለ ወይም የተጣራ ትርፍን ለካፒታል ማሳዳጊያነት ካላዋለው 15% (አሥራ አምስት በመቶ) ሊከፈል የሚገባውን ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት ።

# ከተከፋይ ሂሳቦች ላይ.......

- ስለህብረት ሥራ ማህበራት የግብር አከፋፈል ሁኔታ
  - ስለህብረት ሥራ ማህበራት በወጣው አዋጅ ቁ.985/2009 መሠረት ማንኛውም የህብረት ሥራ ማህበር ካገኘው ትርፍ 30% (ሰላሰ በመቶውን) ለካፒታል ማሳደጊያ ካዋለው በኋላ የቀረውን ትርፍ ግለሰብ ላልሆኑ አባላት የሚያከፋፍል ሲሆን ግለሰብ ላልሆኑ አባላት የሚያከፋለው ትርፍ ከትርፍ ድርሻ ግብር ነጻ ነው፤ ሆኖም ግለሰብ ለሆኑ አባላት የሚከፋፈለው የትርፍ ድርሻ (ሂሳቡ አዲት ተደርጎ) ግብር ይከፍልበታል ፡፡

# ከተከፋይ ሂሳቦች ላይ.......

- የህብረት ሥራ ማህበር አባላት ያገኙትን ትርፍ ለካፒታል ማሳደጊያ የሚያውሉት ከሆነ ይህን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ከህብረት ሥራ ኤጀንሲ ወይም አግባብነት ካለው አካል በማቅረብ ካልተከፋፈለ ትርፍ ግብር ነጻ ሊሆኑ ይችላሉ ፡፡

# ከተከፋይ ሂሳቦች ላይ.......

- በቋሚነት ኢትዮጵያ ውስጥ የሚሰራ ድርጅት ውጭ ለሚገኘው ባለቤት ከሚልከው ትርፍ ላይ የሚከፈል ግብር 15% ይከፍላል፡፡
    - በሠንጠረዥ “ሀ” ፣ “ለ”፣ “ሐ” እና “መ” መሠረት የገቢ ግብር የማይከፈልበት ማንኛውም ገቢ ያገኘ ሰው በጠቅላላ ገቢው ላይ 15% (አስራ አምስት በመቶ) የገቢ ግብር የመክፈል ግዴታ ይኖርበታል ፡፡

# ክፍል ሦስት

## ቅድመ ታክስ /withholding tax/

### 3.1 የቅድመ ታክስ /withholding tax/ ዓላማ

- መንግስት ቅድመ ግብርን በበጀት አመቱ መጨረሻ ከሚሰበስብ ይልቅ ገቢ በተገኘበት ወቅት ሰብስቦ ልማትን ለማፋጠን አመቺ ነው ከሚል እሳቤ /justification/ የመጣ ነው፡፡
- ሻጩ ከሚከፍለው ክፍያ ላይ ግብር ቀንሶ የሚያስቀር ከሆነ ገዥው ሊደብቅ የሚችለውን ግብር በቅድሚያ ለመንግስት እየከፈለ በመሆኑ ቅድመ ታክስ እንደ አንድ መረጃ ጥቅም ላይ ስለሚውል የታክስ ስወራ /tax evasion/ ለመከላከል ይረዳል ፡፡

## 3.2. ዕቃዎች ወደ አገር በሚገቡበት ወቅት ስለሚከፈል ግብር፤

- ለንግድ የሚውሉ ዕቃዎችን ወደ አገር ሲያስገባ የእቃዎቹ የጉምሩክ ዋጋ፣ የመድን አረቦንና የመጓጓዣ ወጪ (CIF) መሰረት በማድረግ 3% የንግድ ስራ ገቢ ግብር በቅድሚያ ለባለስልጣኑ ይከፍላል ፡፡
- ዕቃዎች ወደ አገር በሚገቡበት ጊዜ የቅድሚያ ግብር የሚከፈለው በጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች በኩል ነው ፡፡

## ቅድመ ታክስ /withholding tax/----

**ምሳሌ፡-**

- የ2018 ሞዴል Toyta corolla ዋጋው 6ሺህ ደላር ሲሆን በኢት.ብር 6ሺህ ደላር * 40 ብር 240,000 ብር ፤ የመኪናው ማጓጓዣ 50ሺህ ብር፤ ኢንሹራንስ 1ሺህ ብር ቢከፈል
- 240,000 + 50,000 (Transportation cost) + 1,000 (Insurance) = 291,000.00
- (Cost of goods)
- With holding tax = duty paying value*3 %
- (291,000.00*0.03) = 8730.00 ብር ይሆናል ማለት ነው ።

## 3.3. በሀገር ውስጥ ከሚፈፀሙ ክፍያዎች ላይ ግብር ቀንሶ ስለማስቀረት

### 3.3.1 ግብር ተቀናሽ የሚደረግበት የክፍያ መጠን እና የታክስ መጣኔ

- በሀገር ውስጥ ከሚፈፀሙ ክፍያዎች ላይ ግብር ቀንሶ የማስቀረት ግዴታ የተጣለባቸው ድርጅቶች (ሰዎች) ለሚከተሉት ግብይቶች/አገልግሎቶች ከሚፈጽሙት ጠቅላላ ክፍያ ላይ 3% ግብር ቀንሰው የማስቀረት ግዴታ አለባቸው፡፡

## በሀገር ውስጥ ከሚፈፀሙ ክፍያዎች ላይ...

- በኢትዮጵያ ውስጥ በአንድ ግዥ ወይም በአንድ የዕቃ አቅርቦት ውል ከ20,000 (ሃያ ሺህ) ብር በላይ ለሆነ የዕቃ አቅርቦት ለሚፈፀም ክፍያ እና
- በኢትዮጵያ ውስጥ በአንድ የአገልግሎት ውል ከ10,000 (አሰር ሺህ) ብር በላይ ለሚፈፀም ክፍያ 3% ግብር ቀንሰው የማስቀረት ግዴታ አለባቸው፡፡

- በዕቃና አገልግሎት ግዥ ውል መሠረት ከሚፈፀም ቅድመ ክፍያ (Advance Payment) ላይ የቅድመ ግብር ክፍያ ተቀናሽ አይደረግም ፡፡

- በአንድ ውል ውስጥ የተመለከተው አጠቃላይ የገንዘብ መጠን በተለያየ ጊዜያት ተከፋፍሎ ክፍያ የሚፈፀም ሲሆን ለቅድመ ግብር ክፍያ መሠረት የሚሆነው አጠቃላይ በውሉ ላይ የተመለከተው የገንዘብ መጠን ነው ፡፡

- ግብር ተቀናሽ የሚደረግበት ዕቃ ወይም አገልግሎት አቅራቢ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥሩን እና የፀና የንግድ ስራ ፈቃዱን (ሁለቱንም) ግብር ቀንሶ ለሚያስቀረው ገዢ ሊያቀርብ ካልቻለ ገዢው ለአቅራቢው ከሚፈጽመው ጠቅላላ ክፍያ ላይ 30% (ሰላሳ በመቶ) ግብር ተቀናሽ ማድረግ አለበት ፡፡

- የቤት ኪራይ አገልግሎት እና የግዢ ማረጋገጫ ደረሰኝ (Purchase Voucher) መጠቀም ከሚቻልባቸው ግብይቶች ላይ ተቀናሽ የሚደረገው 3% (ሶስት በመቶ) ቅድመ ግብር ብቻ ነው።
- ተቀናሽ የሚደረገው 3% (ሶስት በመቶ) እና 30% (ሠላሳ በመቶ) ግብር የሚሰላበት የዕቃ ወይም የአገልግሎቱ ጠቅላላ የክፍያ መጠን በግብይቱ ላይ የሚከፈሉ የመንግስት ታክሶችን (እንደ ተጨማሪ እሴት ታክስ  የመሳሰሉትን) እና በሻጭ ገቢ ውስጥ የማይካተቱ ክፍያዎችን ሳይጨምር ነው።

## 3.3.2 ግብር ተቀናሽ የሚደረግበት ለጥገና ወይም ለእድሳት የሚፈፀም የክፍያ መጠን

- የጥገና እና /ወይም የዕድሳት አገልግሎት ሰጪዎች ከአገልግሎት ገዢ ጋር ለጥገና ወይም ለዕድሳት በሚያደርጉት ውል መለዋወጫ ዕቃዎችን አገልግሎት ሰጪ በደረሰኝ ገዝቶ ሲያቀርብ ገዢ ገንዘቡን እንደሚተካለት ከተስማሙ አገልግሎት ሰጪው ለመለዋወጫ ዕቃዎች ግዢ ከሚፈጽመው ክፍያ ላይ ግብር ተቀናሽ አድርጎ ገቢ የማድረጉ ግዴታ እንደተጠበቀ ሆኖ

## በሀገር ውስጥ ከሚፈፀሙ ክፍያዎች ላይ...

- አገልግሎት ሰጪው ለመለዋወጫ ግዥ ያወጣው ገንዘብ በደረሰኙ መሠረት በገዢው ሲተካለት ከተከፋይ ሂሣብ ላይ 3% (ሶስት በመቶ) ግብር ተቀናሽ የማይደረግበት ሲሆን ግብር ተቀናሽ የሚደረገው ከ10,000 ብር በላይ በተከፈለ የአገልግሎት ዋጋ ላይ ብቻ ነው ።

- አገልግሎት ሰጪው ራሱ አገልግሎቱን ከመለዋወጫ ዕቃው ጋር በአንድነት የሚያቀርብ እና ለዚሁ ጠቅላላ ዋጋ የሚከፈለው በሚሆንበት ጊዜ አገልግሎት ሰጪው ከሚያገኘው ጠቅላላ ተከፋይ ሂሣብ ላይ ክፍያውን የፈፀመው ገዢ 3% ግብር ቀንሶ ገቢ ማድረግ አለበት ።
- የጥገና እና እድሳት አገልግሎት ማለት ተሽከርካሪና የተለያዩ ማሽነሪዎች (ሎደር፣ግሬደር የፋብሪካ ማሽኖች የመሳሰሉት) እና የመሳሪያዎች ጥገናና እድሳትን ይጨምራል።

## 3.3.3. የኮንስትራክሽን አገልግሎት ግዢን በሚመለከት

- ለኮንስትራክሽኑ ስራ የሚያስፈልጉ ዕቃዎችን ኮንትራክተሩ የሚያቀርብ በሚሆንበት ውል መሰረት ለኮንትራክተሩ ከሚፈጸም ክፍያ ላይ ግብር ተቀናሽ የሚደረገው እንደ ኮንስትራክሽን ስራው አይነት ከጠቅላላው ክፍያ ቀጥሎ የተመለከተው መቶኛ ብቻ ተወስዶ ይሆናል ፡፡
  - የህንጻ ግንባታ -------------------------------------------45
  - የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት ሲቪል ስራ --------------------50

## በሀገር ውስጥ ከሚፈፀሙ ክፍያዎች ላይ...

- የመንገድ ግንባታ
  - ለጠጠር መንገድ ---------------------------------- 72
- ለአስፋልት መንገድ
  - አስፋልት ኮንክሪት (Gravel Asphalt Concrete)-----65
  - በድርብ አስፋልት (Gravel Double Surface --------60
  - መንገድ ማሻሺያ (Rehabilitation ) ----------------------40
- ድልድይ ስራ -----------------------------------------55

**3.3.4. በሀገር ውስጥ ከሚፈፀሙ ክፍያዎች ላይ ግብር ቀንሰው እንዲያስቀሩ ግዴታ የተጣለባቸው ሰዎች/ድርጅቶች፡-**

- **በህግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው ድርጅቶች፡-** የአክሲዮን ማህበር፣ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር፣ የሽርክና ማህበር፣ ህብረት ስራ ማህበር፣ ...ወዘተ፣
- **የመንግስት መ/ቤቶች፡-** በፌደራል እና በክልል የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ መሠረት ለመንግስት መ/ቤቶች በተሠጠው ትርጉም ውስጥ የሚካተቱ ወይም በተቋቋሙበት ሕግ የመንግስት መ/ቤት የተባሉ የፌዴራል፣ የክልል፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የመንግስት መ/ቤቶች፣

- **የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ድርጅት፡-** በምርት ገበያው አማካኝነት ከሚከናወን ግብይት ጋር በተያያዘ ገዥውን በመወከል የሚፈፅመው ግብይት፣
- **ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶች፡-** ለትርፍ ላልሆነ ለተለያዩ ዓላማዎች የተቋቋሙ ማህበራት፣ የሃይማኖት ድርጅቶች፣
- **መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፡-** በሲቪክ ማህበራት አዋጅ መሰረት የተቋቋሙ የኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም ማኅበሮች ወይም በኢትዮጵያ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ በውጭ አገር የተቋቋሙ ተመሳሳይ ድርጅቶች፣

## 3.3.5. ግብር ቀንሰው እንዲያስቀሩ ግዴታ የተጣለባቸው ግለሰብ ግብር ከፋዮች፣

- የደረጃ “ሀ” ግብር ከፋዮች ባለፉት ሶስት ተከታታይ አመታት በአማካኝ 10 ሚሊዮንና ከዚያ በላይ ጠቅላላ ገቢ ያስመዘገቡ ግለሰብ ግብር ከፋዮች፤
- ዓመታዊ ጠቅላላ ገቢያቸው ከግምት ውስጥ ሳይገባ ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብር ቀንሰው የማስቀረት ግዴታ ያለባቸው የደረጃ “ሀ” ታክስ ከፋዮች፡-
  - ማንኛውም ባለ ኮከብ ሆቴል ወይም ማንኛውም ሪዞርት፣
  - ከ1-4 ደረጃ ያላቸው ስራ ተቋራጮች፣

- ማንኛውም የሪል እስቴት አልሚ፣
- የምግብ አምራች እንዱስትሪዎች፣
- በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ግዥ የሚፈፅም ማንኛውም ግለሰብ ግብር ከፋይ በምርት ገበያው በኩል ላደረገው ግብይት ብቻ፣
- ሆስፒታሎች እና በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር መስፈርት መሠረት ከፍተኛ እና ከዚያ በላይ ደረጃ ያላቸው ክሊኒኮች፣ ዩኒቨርስቲዎችና ኮሌጆች፣
- ከአምራች እንዱስትሪዎች ምርት በመረከብ የሚያከፋፍል ማንኛውም ግለሰብ ግብር ከፋይ ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ቅድመ ግብር በመቀነስ ገቢ የማድረግ ግዴታ አለባቸው።

## 3.3.6 ግብር ቀንሶ የመያዝ ስርዓት ተፈጻሚ የማይደረግባቸው ግብይቶች፡-

- የሰው ወይም የእንስሳት ህክምና አገልግሎት፤የመደበኛ ትምህርት አገልግሎት (ስልጠናን አይጨምርም፤
- የፋይናንስ አገልግሎት(ባንክ የደንበኞቹን ንብረት ሲሸጥ የሚቀበለውን ክፍያ አይጨምርም፤
- የኤሌክትሪክ አገልግሎት፤የቴሌ ኮሚኒኬሽን አገልግሎት፤
- የየብስ፣ የአየር፣ የባህር እና የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት (ኪራይን አይጨምርም)

## በሀገር ውስጥ ከሚፈፀሙ ክፍያዎች ላይ...

- የውሃ አገልግሎት (የታሸገ ውሃን አይጨምርም)፤
- ከገቢ ግብር ነፃ መብት የተሰጣቸው ኢቨስተሮች ከግብር ነፃ በሆኑበት ጊዜ ውስጥ የሚሠጡት አገልግሎት ወይም የሚያቀርቡት ዕቃ፤
- የነዳጅ አቅርቦት ( ቅባትና ዘይቶችን አይጨምርም )፤
- የፋብሪካ ምርት ያልሆነ (የአርብቶ አደር እና የአርሶ አደር የግብርና እና የእንሰሳት ውጤት እንዲሁም ከእንሰሳት የሚገኝ አገልግሎት )፣

## በሀገር ውስጥ ከሚፈፀሙ ክፍያዎች ላይ...

- በፌደራልና በክልል የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ መሠረት ለመንግስት መ/ቤት በተሰጠው ትርጉም ውስጥ የሚካተቱ ወይም በተቋቋመበት ህገ መንግስት የመንግስት መ/ቤት የተባሉ የፌዴራል፣የክልል፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና የድሬዳዋ አስተዳደር መንግስት መ/ቤቶች የሚያቀርቧቸው ዕቃዎችና አገልግሎቶች፤
- ከመንግስት በተሠጣቸው ውክልና መሰረት ዕቃ ወይም አገልግሎት የሚያቀርቡ ድርጅቶች፤

## በሀገር ውስጥ ከሚፈፀሙ ክፍያዎች ላይ…

- በዲፕሎማቲክና ሌሎች ዓለም አቀፍ ስምምነቶች መሠረት ለተቋቋሙ የአለም አቀፍ ድርጅቶች የውጭ ዲፕሎማቲክ ወይም ኮንሱላር ሚስዮኖችና ኢምባሲዎች እና ለተባበሩት መንግስታት አካላት የሚፈጸም ክፍያ፤
- ለትርፍ ያልተቋቋሙ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና ማህበራት የሚያቀርቧቸው ዕቃዎችና አገልግሎቶች ከተቋቋሙበት አላማ ውጪ በንግድ መልክ የሚያቀርቧቸውን ዕቃዎችና አገልግሎቶች አይጨምርም፤

# በሀገር ውስጥ ከሚፈፀሙ ክፍያዎች ላይ...

- በዲፕሎማቲክና ሌሎች ዓለም አቀፍ ስምምነቶች መሠረት ለተቋቋሙ የአለም አቀፍ ድርጅቶች የውጭ ዲፕሎማቲክ ወይም ኮንሱላር ሚስዮኖችና ኢምባሲዎች እና ለተባበሩት መንግስታት አካላት የሚፈጸም ክፍያ፤
- የባህር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ድርጅት ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች የሚፈፅምለት ክፍያ፤

- የመኖሪያ ቤት ሽያጭ፤
- በሰው ጉልበት የሚከናወን ዕቃ የመጫን እና የማውረድ አገልግሎት፣
- ቅይጥ ግብይት (አንድ ግብይት ውስጥ ቅድመ ግብር የሚመለከተውና የማይመለከተው ግዥ)፤
- በማቋቋሚያ ህጋቸው ከገቢ ግብር ነፃ የሆኑ ተቋማትን ሚኒስቴሩ ለሌሎች እቃዎች ወይም አገልግሎቶች ግዢ የሚፈጸም ክፍያ የቅድመ ግብር ክፍያ ስርዓት ተፈጻሚ እንዳይደረግበት ሊወስን ይችላል።

## 3.3.7. ግብሩን ቀንሶ እንዲያስቀር ግዴታ የተጣለበት ሰው ተግባርና ኃላፊነት፡-

- በአገር ውስጥ ከሚፈጸሙ ክፍያዎች ላይ በወሩ ውስጥ ቀንሶ ቀሪ ያደረገውን አጠቃላይ ግብር ከወሩ የመጨረሻ ቀን ጀምሮ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ለባለስልጣኑ ገቢ ማድረግ አለበት።
- ከሚፈጸሙ ክፍያዎች ላይ ቀንሶ ያስቀረውን ግብር ገቢ በሚያደርግበት ጊዜ ክፍያ የተፈፀመለትን እና ግብር የተቀነሰበትን፡-
    - ✓ የእያንዳንዱን ሰው ወይም ድርጅት ስም፤

## በሀገር ውስጥ ከሚፈፀሙ ክፍያዎች ላይ…

- የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር /TIN/፤
- በወሩ ውስጥ ለተጠቀሰው ሰው የተከፈለውን ገንዘብ አጠቃላይ ድምር፣
- ተቀናሽ ተደርጎ የቀረውን ግብር
- በእያንዳንዱ ሰው ስም ለባለስልጣኑ ገቢ የተደረገውን ሂሳብ የሚያሳይ ዝርዝር ባለስልጣኑ በሚያዘጋጀው ቅጽ መሰረት ማቅረብ አለበት፣

## በሀገር ውስጥ ከሚፈፀሙ ክፍያዎች ላይ...

- ✓ ከላይ የተገለፀትን ሰነዶች ኮፒ ባለስልጣኑ በሚሰጠው ቅፅና ሁኔታ እንዲሁም በሚወሰነው የጊዜ ልዩነት እንዲያቀርቡ ሲጠይቅ ማቅረብ፡፡
- ✓ ግብር ቀንሶ የማስቀረት ግዴታ ያለበት ሰው በክፍያ ወቅት ግብር ቀንሶ ሲያስቀር የግብር ከፋዩን ስም አድራሻና የግብር ከፋዩን መለያ ቁጥር በመጠቀም መመዝገብ እና ሂሳቡን በዚሁ መሰረት መያዝ አለበት፡፡
- ✓ ግብር ለተቀነሰበት ሰው ተከታታይ ቁጥር ያለው ደረሰኝ መስጠት፡፡

## 3.3.8 ተቀንሶ ገቢ የተደረገ ግብር ስለማካካስ እና ተመላሽ አፈፃጸም

- ግብር ከፋዩ የግብር ዘመን ካለፈ በኋላ ቀደም ሲል በነበሩት የግብር ዘመናት ያልተቀነሰ ቅድመ ግብር ክፍያ የከፈለ እንደሆነ እንዲሁም ቅድመ ግብሩ ከተከፈለ በኋላ የተገዛው ዕቃ ተመላሽ የተደረገ ወይም የኪራይ ዘመኑ ከመጠናቀቁ በፊት ውሉ የተቋረጠ እንደሆነ በግዥ ወቅት የተከፈለው ቅድመ ግብር በተከፈለበት ግብር ዘመን ለሚፈለግበት የኪራይ ገቢ ወይም የንግድ ትርፍ ግብር ማካካሻ ይውላል።

## በሀገር ውስጥ ከሚፈፀሙ ክፍያዎች ላይ…

- ግብር ከፋዩ በብልጫ የተከፈለ የቅድሚያ ግብር ክፍያ ተመላሽ ሲጠይቅ ባለስልጣኑ በግብር ከፋዩ የቀረበው የሂሳብ መግለጫ ዕውቅና በተሰጠው የውጭ ኦዲተር የተመረመረ መሆኑን በማጣራት እና ግብር ከፋዩ ያቀረባቸው የይካካስልኝ ወይም የይመለስልኝ ጥያቄ በደጋፊ ሰነድ የተደገፈና የቅድመ ታክስ ክፍያው ዝርዝር መረጃ ሲያቀርብ፤

## በሀገር ውስጥ ከሚፈፀሙ ክፍያዎች ላይ...

- የሂሳብ መዝገብ ለማይዝ ወይም የሂሳብ መዝገቡ ውድቅ ለሆነ ግብር ከፋይ ዕቃዎች ወደ ሀገር በሚገቡበት ጊዜ እና በሀገር ውስጥ ከሚፈፀሙ ክፍያዎች ላይ ተቀንሶ በቅድሚያ የተከፈለ ግብር እና በዚያው የግብር ዓመቱ ተከፋፍሎ ለባለስልጠኑ ገቢ የተደረገ ግብር ካለ በሚቀርበው ማስረጃ መሰረት ይቀነሳል።

## ***3.3.9*** ከቅድመ ግብር ጋር የተያያዙ አስተዳደራዊ ቅጣቶች

- በፌደራል ገቢ ግብር አዋጅ *979/2008* በተደነገገው መሰረት ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ታክስ ቀንሶ ለባለስልጣኑ ማስተላለፍ ያለበት ማንኛውም ሰው ሳይቀንስ የቀረውን ወይም ቀንሶ ለባለስልጣኑ ያላስተላለፈውን ታክስ *10%* (አስር በመቶ) ቅጣት ይከፍላል።

## በሀገር ውስጥ ከሚፈፀሙ ክፍያዎች ላይ...

- የታክስ ማስታወቂያ ግዴታውን ያልተወጣ ግብር ከፋይ ወይም ዘግይቶ ታክሱን ያሳወቀ ግብር ከፋይ ለዘገየበት ለዕያዳንዱ የታክስ ጊዜ ወይም ከፊል ለሆነው ጊዜ ያልተከፈለውን ታክስ 5% (አምስት በመቶ) የሚከፍል ሲሆን ይህ የቅጣት ክፍያ የሚከፈለው 25% (ሃያ አምስት በመቶ) እስከሚሞላ ድረስ ይሆናል፡፡

## በሀገር ውስጥ ከሚፈፀሙ ክፍያዎች ላይ…

- ማንኛውም ታክስ ከፋይ በታክስ መክፈያ ጊዜ ውስጥ ታክስ ሳይከፍል ከቀረ ለዘገየበት ጊዜ
    - ለአንድ ወር ወይም የወሩ ክፊል ለሆነው ጊዜ ባልተከፈለው ታክስ ላይ 5 (አምስት በመቶ እና
    - ከዚያ በኋላ ለዘገየበት ለዕያንዳንዱ ወር ወይም የወሩ ክፊል ለሆነው ጊዜ ባልተከፈለው ታክስ ላይ ተጨማሪ 2% (ሁለት በመቶ) ቅጣት ይከፍላል

- ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ታክስ ቀንሶ የመያዝ ግዴታ ያለበት ታክስ ከፋይ ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ታክስ ቀንሶ ያላስቀረ እንደሆነ ወለድ እና ቅጣትን ሳይጨምር ሳይቀንስ የቀረውን ታክስ ከአቅራቢው የማስመለስ መብት አለው።
- ለድርጅት በሚሆንበት ጊዜ በድርጅቱ ላይ የሚጣለው ቅጣት እንደተጠበቀ ሆኖ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ፣ ዋና የሂሳብ ሹም ወይም ታክስ ተቀንሶ መያዝ እንዳለበትና የማረጋገጥ ኃላፊነት ያለበት ማንኛውም ሌላ የድርጅቱ ሰራተኛ እያንዳንዳቸው ብር 2,000 (ሁለት ሺህ ብር) ቅጣት ይከፍላሉ።

# በሀገር ውስጥ ከሚፈፀሙ ክፍያዎች ላይ…

- ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብር ቀንሰው እንዲያስቀሩ ኃላፊነት የተሰጣቸው ድርጅቶች ወይም ግለሰብ ግብር ከፋዮች ኃላፊነታቸውን በአግባቡ ካልተወጡ አቅራቢውና ገዥው እያንዳንዳቸው 20,000 (ሃያ ሺህ ) ብር ቅጣት ይከፍላሉ።
- ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ የሚከፈልን ታክስ ለማስቀረት በማሰብ ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ታክስ ቀንሶ የመክፈል ግዴታ ላለበት ሰው እቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን ለማቅረብ ፈቃደኛ ያልሆነ ሰው 10,000 (አስር ሺህ) ብር ቅጣት ይከፍላል፡፡

# በሀገር ውስጥ ከሚፈፀሙ ክፍያዎች ላይ...

ምሳሌ፡-

ኤቢ ኃላ.የተ.የግል.ማህበር የበጎ አድራጎት ድርጅቶች በአዲስ አበባ ከተማ ከሚገኝ “ዜድ” ከተባለ የጨርቃጨርቅ አምራች ድርጅትጋር ለሰራተኞቻቸው የ400,000 ብር የደንብ ልብስ ግዥ ቢፈፅሙ ሻጩ/አቅራቢው የእጅ በእጅ የሽያጭ ደረሰኝ ወይም የካሽ-ሬጂስተር ደረሰኝ ከሰጣቸው ከሚከፍሉት ክፍያ ላይ 3% ቀንሰው በማስቀረት ለባለስልጣኑ ዊዝሆልድንግ ታክስ መክፈል አለባቸው ማለት ነው።

## በሀገር ውስጥ ከሚፈፀሙ ክፍያዎች ላይ...

- በዚህ መሠረት የ400,000.00 ብር 3% 12,000.00 ብር ይሆናል፤ስለዚህ ገዥዎቹ ወገኖች ለሻጩ ከሚከፍሉት ክፍያ ላይ 12,000 ብር በማስቀረት 12ሺውን ለመንግስት ግብር እንዲሁም (400,000.00 ብር - 12,000.00) ብር388,000.00 ለገዥው መክፈል አለባቸው ማለት ነው።
- ሆኖም ግን ሻጭ የታክስ መለያ ቁጥሩን እና የፀና ንግድ ፈቃድ ካልሰጠ የግዥውን ጠቅላላ ክፍያ 400,000*30% = ብር120,000 ለመንግስት ግብር እንዲሁም 400,000-120,000 = 280,000 ብር ለሻጭው መክፈል ይኖርበታል ማለት ነው።

# ሙከራ

1. ከተከፋይ ሂሳብ ቀንሶ ገቢ የሚያደርጉ ሰዎች/ ድርጅቶችን ዘርዝር

2. ከተከፋይ ሂሳቦች ቀንሶ መያዝ የማይመለከታቸው ግብይቶችን ዘርዝር

- ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብርን ቀንሶ የማስቀረት ሥርዓት ግብር ከሚሰበሰብባቸው መንገዶች አንዱ ነው። ከተከፋይ ሂሳቦች ግብር ቀንሶ ማስቀረት ሥርዓትን ቀርጾ መተግበር መንግሥት ለህበረተሰቡ የሚያቀርባቸውን የልማት ሥራዎች/ አገልግሎቶች ወጪ መሸፈኛ የሚሆን ገንዘብ በየጊዜው እንዲሰበሰብ ለማድረግ ከመሆኑ በተጨማሪ ስለሽያጭና ገዥ ምንጭ እንዲኖር ያደርጋል ።

- ይህን ቀላል የታክስ አሰባሰብ ሥርዓት ውጤታማ ለማድረግ ግብር ከፋዩ ግብሩን በወቅቱና በአግባቡ በመክፈል፣ ታክሱን የመሰብሰብ ኃላፊነት የተጣለባቸው አካላት ታክሱን በአግባቡ ሰብስበው በወቅቱ ለግብር አስገቢው መ/ቤት ፈሰስ ለማድረግ ይችል ዘንድ የግብር ሰብሳቢው ባለሥልጣንም ለታክሱ አሰባሰብ ምቹ የሆኑ መመሪያዎች እና አሰራሮችን በመቅረጽ፣ ለግብር ከፋዩ ቀጣይነት ያለው ግንዛቤ በመፍጠር፣ ሆነ ብለው በህገወጥ መንገድ የሚሄዱትንም በመለየት ህጋዊ ርምጃ በመውሰድ በጋራና በትብብር ሊሰሩ ይገባል።

## ማጣቀሻዎች (የመረጃ ምንጭ)

1. የገቢ ግብር አዋጅ ቁ.979/2008

2. ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁ. 983/2008

3. የገቢ ግብር ደንብ ቁ 410/2009

4. የታክስ አስተዳደር ደንብ 407/2009

5. የቅድመ ገብር ክፍያ ሥርዓት አፈጻጸም ቁ.2/2011

6. ከተከፋ ሂሳብ ላይ የንግድ ትርፍ ግብር ቀንሰው እንዲያስቀሩ ኀላፊነት የተሰጣቸው 7. ግለሰብ ታክስ ከፋዮችን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁ. 145/2011

8. ባልተከፋፈለ ትርፍ ላይ ስለተጣለው ግብር አፈጻጸም የወጣ መመሪያ ቁ.7/2011

9. የካፒታል ሀብቶችን በማስተላለፍ በሚገኝ ጥቅም ላይ ስለሚከፈል

# አመሰግናለሁ!

Email: morethiopia@gmail.com